March 24 2016
መጋቢት 15 2008 ዓም

# ምስጋና





**ተኮላ ወርቁ  ንጉሱ ታምራት    ወርቁ መንገሻ  ወርቁ ሞላ    ይትባረክ ወንድምአገኝ ቴውድሮስ በቀለ**

ክቡር ለሆነው ለሰው ልጅ ነፃነት፣ ለፍትህ፣ ለአንድነት ሉዓላዊነቷ ለተከበረች ኢትዮጵያ ፣ በዘላቂነት ለማገልገል የተቋቋመው በስዊድን የኢትዮጵያ አንድነት ራድዮ በፕሮፌሽናል ጆርናሊዝም አሶሴየሽን በአሜሪካና ዓለም አቀፍ (OEJICUSA) መመረጡን ምክንያት በማድረግ መዋቅሩ / ኰሚቴው የላከለትን ስጦታ ሲቀበል ከታላቅ አክብሮትና ከምስጋናም ጋር ጭምር ነው። በአሜሪካና ዓለም አቀፍ ደረጃ ዕውቅና ባላቸው ታዋቂ የሆኑ ባለሙያዎችን ባሰባሰበና መገናኛ ብዙሃን ግልፅነት፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት አብቦ የኢንፎርሜሽን / መረጃ ተዳራሹ ሕብረተሰብ የዕውቀት አድማስ የሚሰፋበትን ዕይታ የሚያበረታታው ኰሚቴ በስዊድን የኢትዮጵያ አንድነት ራድዮን ተግባሮች ፈትሾ የ2015 ዓ ም ተሻላሚ ማድረጉ የኢትዮጵያዊነት ድምፅ አለምት አቀፍ አጋር እንዳለው አረጋግጧል።

የኢትዮጵያ አንድነት ራድዮ በስዊድን ከተመሰረተ እንሆ በዚህ ዓመት 8 ኛ አመቱን ይሞላል። ለኢትዮጵያ ሕዝብ የነፃነት ትግል ቀንዲል በመሆን የዲሞክራሲ ትግል *በአንድ አገር፣ በአንድ ሕዝብ፣ በአንዲት ሰንደቅ ዓላማ* በሚለው መርሆና የአንድነት መንፈስ ከነፃ ህሊና ጋር የታረቀ የዕውነት ልሳን በመሆን ለሚያደርጋቸው አስተዋፅኦዎች አድናቆትን ማትረፉ የሬድዮኑ የቦርድ አባላት፣ የሥርጭቱ ባልደረቦችና ደጋፊዎች ከፍ ያለ ኩራት ይሰማቸዋል።

በስዊድን የኢትዮጵያ አንድነት ራድዮ እና የኢትዮፓትርዮትስ ድህረገፅ ከዘረኞች እና ከከፋፋዮች ነፃ ወጥታ በልጆቿ ተመክታና ኰርታ ሁሉም ዜጋ በሰላም፣ በአንድነት፣ በፍቅር በዲሞክራሲ የሚኖርባት ለማድረግ በሚደረገው ትግል ወገንተኛነታቸውን እየገለጹ፣ለትግሉ ዋልታና ማገር የሆኑትን፣ ለመሆንም የሚነሳሱትን ምሁራኖች፣ አገር ወዳጆች፣ ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች ጋራ በመደጋገፍ የሚያበረክቱትን አስተዋፅኦ የጣለባቸውን አደራ ግዴታውንና ሐላፊነቱን እንደሚወጡ ቃል ይገባል።




ይህን መሰል የማበረታቻ  ስጦታ ከፍተኛ የሆነ የትግል ወኔ እንደሚሰጠን እና በቁሳዊ ጥቅም ክፍያዎች የተገነባ መሰባሰብ ሳይሆን በነፃ ህሊናችን ላይ በመቆም ከሁሉ በላይ ኢትዮጵያዊነትን ማስቀደም በሚለው መርሆ ዙርያ ለመስራት የገባነውን ቃል እንድናጸናና እንድንጠበቅ ድጋፍ በመሆናቸሁ የኰሚቴውን (OEJICUSA) ምርጥ አባላትና  የመዋቅሩን በጐ ተልዕኰ ከልብ እናመሰግናለን፡፡ ኢትዮጵያዊነት ተጠቃሚ የሚሆንበት ሜድያ መፍጠር ታላቅ አኩሪ ተግባርና ዘላቂ ዓላማችን መሆኑን በዚሁ አጋጣሚ እንገልፃለን።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!

በስዊድን የኢትዮጵያ አንድነት ራድዮ አባላት
የኢትዮፓትርዮትስ ድህረገፅ የህትመት ክፍል